
# ዜና አዲስ ፀረ-ሙስና

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን
Addis Ababa city administration Ethics & Anti- corruption commission
2015

ቅጽ 2 ቁጥር 3

የካቲት 2017


## በለውጡ ሂደት በፀረ-ሙስና ትግል የተገኘው ውጤት ዘላቂ እንዲሆን የህብረተሰቡ ተሳትፎ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል - ከንቲባ አዳነች አቤቤ





የንቅናቄ መድረክ በተካሄደበት ወቅት

በለውጡ ሂደት በፀረ-ሙስና ትግል የተገኘው ውጤት ዘላቂ እንዲሆን የህብረተሰቡ ተሳትፎ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

የአዲስ አበባ ከተማ ሥነ ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን 21ኛውን ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን ምክንያት በማድረግ ከተማ አቀፍ የንቅናቄ መድረክ አካሂዷል።

እለቱም "ወጣቶችን ያማከለ የፀረ-ሙስና ትግል፣ የነገ ስብዕና ይገነባል!" በሚል መሪ ሀሳብ የተከበረ ሲሆን፥ የመዲናዋ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎች፣ ወጣቶችና የተለያዩ ማህበራት ተሳትፈዋል።

በሀገር፣ በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሙስና ያለበት ደረጃ ላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ጽሁፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

## ሙስናን በዘላቂነት ለመከላከል ትውልድን በስነ ምግባር መገንባት ያስፈልጋል

አዲስ አበባ፤ህዳር 27/2017(ኢዜአ)፥ሙስናን በዘላቂነት ለመከላከል ትውልድን በስነ ምግባር መገንባት እንደሚገባ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ ምህረቱ ሻንቆ(ዶ/ር) ገለጹ።

የአዲስ አበባ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ጋር በመተባበር "ስነ ምግባራዊ ትውልድ ለሁለንተናዊ ብልጽግና" በሚል መሪ ሀሳብ ያዘጋጁት የፓናል ውይይት በዓድዋ ድል መታሰቢያ ተካሂዷል።

በመድረኩ ከሙስና የጸዳ ከተማ እና ሀገር ለመፍጠር በሚደረገው ሂደት ውስጥ ህብረተሰቡ ሙስናን ለመከላከል አጋዥ እንዲሆን የጋራ አረዳድ ለመፍጠር ያለመ መሆኑ ተመላክቷል።

ወደ ገጽ 9 ዞሯል




ኮሚሽነር ጀማል ረዲ የፓናል ውይይቱን በከፈቱበት ወቅት

**ሙስና ስጋት የማይሆንባት አዲስ አበባን እንፈጥራለን!**

# በስነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራት የትምህርት ማህበረሰቡ ሚና

የትምህርት ተቋማት በስነ ምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራት የሚያደርጉት ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት ስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች በአንደኛ፣ ሁለተኛ ደረጃና በከተማ አስተዳደሩ በጀት በሚተዳደሩ ኮሌጆች ለሚማሩ ተማሪዎች የሚሰጠው የስነ ምግባርና ጸረ-ሙስና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተጠናክረው ቀጥለዋል፡፡

የጸረ-ሙስና ክበብን በማጠናከ ሙስናን በመከላከሉ በኩል ኃላፊነታቸውን መወጣት ይገባቸዋል፡፡

የግንዛቤ ማስጨበጫው የነገ ሀገር ተረካቢ የሆነውን ትውልድ ከመሰረቱ በሌብነት ምንነት፣ ሌብነት በሀገርና በትውልድ ላይ የሚያመጣውን ጉዳት በማስገንዘብ ሙስናን የሚጠየፍና በስነ ምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራት ያለመ ነው፡፡ በተጨማሪም በንቅናቄ መድረኮች ላይ የትምህርት




የተማሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ በከፊል

የኮሌጅ፣ የክፍለ ከተማና የወረዳ የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች የተማሪዎች የስነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ክበባት በማደራጀት፣ የተለያዩ ፕሮግራም በማዘጋጀትና በሰልፍ ስነ ሥርዓት ላይ በመገኘት ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የስነ ምግባር መርሆችን እንዲከተሉ በማስገንዘብ ተማሪዎች ሙስናን እንዲጠየፉ በማድረግ በትኩረት እየተሰራ በመሆኑ ሁሉም የትምህርት ማህበረሰቡ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡

ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ በውጭ ስለ ሙስና አስከፊነት ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ተግባራትን በማከናወንና ቤቶች ዋና ዓላማ በተማሪዎች ላይ አዎንታዊ የባህሪ ለውጥ ማምጣት ሲሆን በእውቀት፣ በክህሎት እና በስነ ምግባር የጎለበተ ሀገር ተረካቢ ትውልድን ማፍራት መሆኑን ተብራርቷል፡፡

ተማሪዎች ሊያጎለብቷቸው የሚገቡ የስነ ምግባር መርሆዎች ቅንነትን፣ እውነት መናገርን፣ ቃልን ማክበር፣ ታማኝነትን፣ ከአድሎ መራቅን /ፍትሃዊነትን፣ ህግን ማክበር፣ የባልድረቦችን ክብር መጠበቅ፣ ተጠያቂነትንና ሌሎችንም እሴቶችን በማዳበር ለሀገራችን ብቁ ዜጋ መሆን እንዳለባቸው ተብራርቷል፡፡

"በኮሚሽኑ ያሉ መልካም የስራ ባህሎችን.....

ከገጽ 4 የዞረ

ስራዎችን መስራቱን ገልፀው ለዚህ ደግሞ የአመራሩና የባለሙያው ቅንጅት የተሻለ መሆኑን የሚያሳይ ነው ብለዋል፡፡ ምክትል ኮሚሽነሯ አክለዉም በቀጣይ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በማሳደግ የፀረ ሙስና ትግሉ ውጤታማ ማድረግ ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በዕለቱም ኮሚሽኑ በ2017 በጀት አመት ከማዕከል እስከ ወረዳ ድረስ መከናወን የሚገባቸው ዋና ዋና ተግባራት ለሠራተኛው በዝርዝር ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ በመድረኩ ላይ በርካታ ጥያቄዎችና አስተያየቶች የተነሱ ሲሆን በኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ማብራሪያ ተሠጥቶበታል፡፡

"ኮሚሽኑ ከትምህርት ቢሮ ጋር በቅንጅት.....

ከገጽ 10 የዞረ

እንዲሰሩ በማገዝ፣ እንደዚሁም ተማሪዎች ሊያጎለብቷቸው የሚገቡ የስነ ምግባር መርሆዎች 350 ሮል አፕ ባነሮች አዘጋጅቶ በማሰራጨት በተጨማሪም በስነ ምግባራቸው ምስጉን የሆኑ ሞዴል ተማሪዎችንም እውቅና የመስጠትና የማበረታታት ስራዎችም በመስራት ላበረከተው አስተዋፅዖ ዕውቅናው መሰጠቱን ከመድረኩ ላይ ተመላክቷል፡፡

ኮሚሽኑ በቀጣይ በ2017 በጀት አመት ከቢሮው ጋር የሚሰራበትን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል፡፡

# ዓለም አቀፉን የፀረ-ሙስና በዓል በተቀናጀ የንቅናቄ ስራዎች ውጤታማ ማድረግ እንደሚገባ ተጠቆመ፤



የክብረ በዓሉ ዕቅድ ሲገመገም

ኮሚሽኑ የ21ኛው ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና በዓል አከባበር ማስፈፀሚያ ዕቅድ ላይ ከከተማና ክፍለ ከተማ አፈ ጉባኤዎች እና ፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊዎች ጋር ውይይት አካሄደ።

በውይይቱ የተገኙት በብልፅግና ፓርቲ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ አቶ አለማየሁ እጅጉ የዘንድሮውን በዓል ከሌላው ጊዜ የሚለየው ከተማ አስተዳደሩ የአገልግሎት አሰጣጥ፤ ብልሹ አሰራር እና መልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት በቁርጠኝነት እየሰራ ባለበት ወቅት መሆኑን ተናግረዋል። አክለውም ዓለም አቀፉን የፀረ-ሙስና በዓል በሁሉም መዋቅር የተቀናጀ የንቅናቄ ስራዎች ውጤታማ ለማድረግ ይሰራል ሲሉ ኃላፊው ገልፀዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ በሚፈጠሩ የንቅናቄ መድረኮች የህብረተሰቡ ግንዛቤ በማደጉ በሙስናና ብልሹ አሰራር የሚቀርቡ ጥቆማዎች በመጨመሩ የህዝብና የመንግስት ሀብት ማዳን ተችሏል ብለዋል። የዘንድሮውን በዓል በተለያዩ መድረኮችና ሁነቶች በማክበር ወጣቶች በሀገራቸው ያላቸውን ህልምና ጉጉት እንዲያሳኩ በሙስናና ብልሹ አሰራር መከላከል ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይረዳል ሲሉ ኮሚሽነሩ ጠቅሰዋል።

በመድረኩ የ21ኛው ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና በዓል አከባበር ማስፈፀሚያ ዕቅድ እና የትኩረት አቅጣጫ የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር መቅደስ ተስፋዬ አቅርበዋል። ሀገራችን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን በመፈረም እየሰራች ሲሆን



የክብረ በዓሉ ዕቅድ ሲገመገም

የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ጉዳይ አንገብጋቢና ትኩረት የሚሰጠው በመሆኑ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች በተለየ ትኩረት መስራትና በዓሉን በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ርብርብ እንዲያደርጉ በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የሰላም ፍትህና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ሙሉነህ ደሳለኝ ጥሪ አስተላልፈዋል።

የፀረ-ሙስና ትግሉ በአንድ አካል ብቻ የሚሳካ ባለመሆኑ ተቀናጅተን መስራት አለብን ሲሉ ም/ኮሚሽነሯ ተናግረዋል። የበዓሉን ንቅናቄ በተሳካ ሁኔታ ለማስፈፀም የተለያዩ ተቋማትና አደረጃጀቶችን በማሳተፍ ወጣቶችና ህብረተሰቡን የትግሉ ባለቤት ለማድረግ እንደሚሰሩ በውይይቱ የተሳተፉ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል።

# በኮሚሽኑ ያሉ መልካም የስራ ባህሎችን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ ተገለፀ።





የውይይት ተሳታፊዎች በከፊል

የአዲስ አበባ ከተማ ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የ2016 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም እና የ2017 ዓ.ም እቅድ ላይ ከኮሚሽኑ አመራርና ሠራተኞች ጋር ውይይት አካሄደ።

የአዲስ አበባ ከተማ ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ እንደገለፁት በኮሚሽኑ ያሉ መልካም የስራ ባህሎችን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ ተናግረዋል። አያይዘውም የኮሚሽናችን ትልቁ ተልዕኮ ለሙስና ቀዳዳ የማይከፍት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋትና የማስፈፀም አቅም ግንባታ ማሳደግ ዋና ዋናዎቹ ናቸው ብለዋል።

**ተቋሙ ቅድመ መከላከል ላይ አተኩሮ እየሰራ መሆኑን የገለፁት ምክትል ኮሚሽነር ዘገየ በላይነህ ሲሆኑ የቅድመ መከላከል ሥራውን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት እንዲያስችል የተቋማት የሙስና ተጋላጭነት ደረጃ በየጊዜው እየለየን መሄድ ይኖርብናል ብለዋል። አያይዘዉም የሙስና ተግባራትን መከላከል የአንድ ተቋም ተግባር ብቻ ስላልሆነ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላትና ተቋማት ጋር እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ገልፀዋል።**

**የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር መቅደስ ተስፋዬ በበኩላቸዉ ኮሚሽኑ ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ቢሆነውም በትውልድ ስነ ምግባር ግንባታና ሙስናን በመከላከል ረገድ ውጤታማ**

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የኮሚሽኑን ተልዕኮ ለማሳካት የባለድርሻ አካላት ሚና የጎላ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ከሰባት ባለድርሻ አካላት ጋር ሙስናን በተቀናጀ መልኩ ለመግታት የሚያስችል ስምምነት ተፈራረመ።

ስምምነቱ በዋናነት በትውልድ ስነ ምግባር ግንባታ፣ በከተማችን የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ላይ እየተሰራ የሚገኘውን ስራ አጠናክሮ ለመቀጠል ያለመ መሆኑ ተገልጿል።

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ጀማል ረዲ በቀጣይ የከተማችን የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመከላከል ረገድ ባለድርሻ አካላት ሚና የጎላ መሆኑን ጠቅሰዋል። ኮሚሽነር ጀማል አያይዘውም የትውልድ ስነ ምግባር ግንባታ እና ሙስናን መከላከል ላይ የተጀመሩ ስራዎችን አጠናክሮ ለማስቀጠል የጋራ የስምምነት ሰነድ ተፈራርሞ ወደ ስራ መግባት አስፈላጊ ነው ሲሉም ገልፀዋል።





የስምምነት ሰነድ በተፈረመበት ወቅት

መድረኩ በዋናነት በትውልድ ስነ ምግባር ግንባታ፣ በከተማችን የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ላይ እየተሰራ የሚገኘውን ስራ አጠናክሮ በማስቀጠል የከተማችንን የልማት ጉዞ ማፋጠን እንደሚገባ በመድረኩ ላይ ተመላክቷል።

ኮሚሽኑ በዛሬው ዕለት ከከተማው ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀይል ቢሮ፣ ትምህርት ቢሮ፣ ፍትህ ቢሮ፣ ስራ እና ክህሎት፣ አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ፣ ኢዜአ፣ አዲስ አበባ ከተማ ዋና ኦዲተር፣ የአዲስ አበባ ሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጋር የስምምነት ሰነድ ተፈራርሟል።

# የመከታተያ ክፍሎች የተቋማት አገልግሎቶች ፍትሃዊና ቀልጣፋ እንዲሆኑ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል።



የስልጠናው ተሳታፊዎች በከፊል

ኮሚሽኑ በሙስና መከላከል አሰራር ጥናት፤ በሙስና ተጋላጭነት ጥናት፣ በጥናት ትግበራ ክትትልና ግምገማ አፈፃፀምና በሀብት ምዝገባ ዙሪያ በየደረጃው ለሚገኙ የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች በሁለት ዙር ስልጠና ሰጥቷል።

በስልጠናው የተገኘው እውቀት ለሙስና መከላከል ስራ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ በየተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶች ፍትሃዊና ቀልጣፋ እንዲሁም ከብልሹ አሰራር የፀዱ ሊሆኑ ይገባል ሲሉ የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር መቅደስ ተስፋዬ ገልፀዋል። ይህ እንዲሆን ደግሞ ሁሉም የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ኮሚሽነሯ አሳስበዋል።

በሚሰሩ ስራዎች አቅም እንደሚሆንና በየተቋማቱ ያጋጥም የነበረውን የሙስና ተጋላጭነት አሰራር ጥናት ችግር የሚፈታ ነው ብለዋል። አክለውም የህብረተሰቡንና የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ በማሳደግና ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማድረግ በትውልድ ስነ ምግባር ግንባታና በፀረ-ሙስና መከላከል ውጤታማ ስራዎች እንደሚሰራ አመላክተዋል።

የሙስና ተጋላጭነት ጥናት በሚጠናበት ወቅት አውዳዊነትን፣ አሳታፊነትን፣ ወቅታዊነትና ቀጣይነትን፣ ቀልጣፋና ውጤታማነትን የተከተለ መሆን እንዳለበት እና በየተቋሙ የሚገኙ የመንግሥት ሰራተኞች ሀብት ምዝገባ ስራ በተቀመጠው ጊዜ መፈፀምና



ከዚህ ቀደም በኮሚሽኑ ሲሰሩ የነበሩ ስራዎች ውጤታማ የሆኑት ከላይ እስከታች ያለው አመራርና ባለሙያ በመናበብና ቅንጅት በመፈጠሩ መሆኑን የገለፁት ምክትል ኮሚሽነሯ በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ገልፀዋል።

የኮሚሽኑ የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ስልጠና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጀንበሩ ኢርኮ ስልጠናው የሙስና መከላከል ስራን በጥናትና በዕውቀት ለመለየት እንዲሁም በቀጣይ በማያስመዘግቡት ላይ ደግሞ በአዋጁ መሰረት የተጠያቂነት አሰራር መዘርጋት እንዳለበት በመድረኩ ላይ ተመላክቷል።

በስልጠናው ላይ የሴክተር፣ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ የኮሌጅ፣ የሆስፒታል፣ የክፍለ ከተማና የወረዳ የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍል ዳይሬክተሮችና ቡድን መሪዎች ተሳታፊ ሆነዋል።

# በስነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራት የትምህርት ማህበረሰቡ ሚና

የትምህርት ተቋማት በስነ ምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራት የሚያደርጉት ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል።

በተያዘው በጀት ዓመት ስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች በአንደኛ፣ ሁለተኛ ደረጃና በከተማ አስተዳደሩ በጀት በሚተዳደሩ ኮሌጆች ለሚማሩ ተማሪዎች የሚሰጠው የስነ ምግባርና ጸረ-ሙስና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተጠናክረው ቀጥለዋል።

የጸረ-ሙስና ክበብን በማጠናከ ሙስናን በመከላከሉ በኩል ኃላፊነታቸውን መወጣት ይገባቸዋል።

የግንዛቤ ማስጨበጫው የነገ ሀገር ተረካቢ የሆነውን ትውልድ ከመሰረቱ በሌብነት ምንነት፣ ሌብነት በሀገርና በትውልድ ላይ የሚያመጣውን ጉዳት በማስገንዘብ ሙስናን የሚጠየፍና በስነምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራት ያለመ ነው። በተጨማሪም በንቅናቄ መድረኮች ላይ የትምህርት




የተማሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ በከፊል

የኮሌጅ፣ የክፍለ ከተማና የወረዳ የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች የተማሪዎች የስነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ክበባት በማደራጀት፣ የተለያዩ ፕሮግራም በማዘጋጀትና በሰልፍ ስነ ሥርዓት ላይ በመገኘት ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የስነ መግባር መርሆችን እንዲከተሉ በማስገንዘብ ተማሪዎች ሙስናን እንዲጠየፉ በማድረግ በትኩረት እየተሰራ በመሆኑ ሁሉም የትምህርት ማህበረሰቡ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል።

ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ በውጭ ስለ ሙስና አስከፊነት ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ተግባራትን በማከናወንና ቤቶች ዋና ዓላማ በተማሪዎች ላይ አዎንታዊ የባህሪ ለውጥ ማምጣት ሲሆን በእውቀት፣ በክህሎት እና በስነ ምግባር የጎለበተ ሀገር ተረካቢ ትውልድን ማፍራት መሆኑን ተብራርቷል።

ተማሪዎች ሊያጎለብቷቸው የሚገቡ የስነ ምግባር መርሆዎች ቅንነትን፣ እወነት መናገርን፣ ቃልን ማክበር፣ ታማኝነትን፣ ከአድሎ መራቅን /ፍትሃዊነትን፣ ህግን ማክበር፣ የባለድረቦችን ክብር መጠበቅ ተጠያቂነትንና ሌሎችንም እሴቶችን በማዳበር ለሀገራችን ብቁ ዜጋ መሆን እንዳለባቸው ተብራርቷል።

"በኮሚሽኑ ያሉ መልካም የስራ ባህሎችን.....

ከገጽ 4 የዞረ

ስራዎችን መስራቱን ገልፀው ለዚህ ደግሞ የአመራሩና የባለሙያው ቅንጅት የተሻለ መሆኑን የሚያሳይ ነው ብለዋል። ምክትል ኮሚሽነሯ አክለዉም በቀጣይ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በማሳደግ የፀረ ሙስና ትግሉ ውጤታማ ማድረግ ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

በዕለቱም ኮሚሽኑ በ2017 በጀት አመት ከማዕከል እስከ ወረዳ ድረስ መከናውን የሚገባቸው ዋና ዋና ተግባራት ለሠራተኛው በዝርዝር ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል። በመድረኩ ላይ በርካታ ጥያቄዎችና አስተያየቶች የተነሱ ሲሆን በኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ማብራሪያ ተሠጥቶበታል።

"ኮሚሽኑ ከትምህርት ቢሮ ጋር በቅንጅት.....

ከገጽ 10 የዞረ

እንዲሰሩ በማገዝ፣ እንደዚሁም ተማሪዎች ሊያጎለብቷቸው የሚገቡ የስነ ምግባር መርሆዎች 350 ሮል አፕ ባነሮች አዘጋጅቶ በማሰራጨት በተጨማሪም በስነምግባራቸው ምስጉን የሆኑ ሞዴል ተማሪዎችንም እውቅና የመስጠትና የማበረታታት ስራዎችም በመስራት ላበረከተው አስተዋፅዖ ዕውቅናው መሰጠቱን ከመድረኩ ላይ ተመላክቷል።

ኮሚሽኑ በቀጣይ በ2017 በጀት አመት ከቢሮው ጋር የሚሰራበትን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል።

# የደንብ ማስከበር ኦፊሰሮች ሙያዊ ስነ ምግባር በመላበስ ማገልገል እንደሚገባቸው ተገለፀ።



የስልጠናው ተሳታፊዎች በከፊል

የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለስልጣን የፓራ ሚሊተሪ ኦፊሰሮች በሙያዊ ስነ ምግባር ማገልገል እንደሚጠበቅባቸው ገለፀ።

የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ከስነ ምግባር ፀረ ሙስና ኮሚሽን ጋር በመተባበር በሁሉም ክፍለ ከተማ እና ወረዳ ለሚገኙ 6200 የደንብ ማስከበር (የፖራ ሚሊተሪ) ኦፊሰሮች የስነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 3/2015 እና ሙስናን መከላከል ጨምሮ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ስልጠና ሰጥቷል።

ለፓራ ሚሊተሪ ኦፊሰሮች የስነ-ምግባር መመሪያ እና ብልሹ አሰራር በሀገር ላይ የሚያደርሰው ጉዳቶች አስመልክቶ የተሰጠው ስልጠና ግንዛቤ ከመፍጠር ባሻገር በቀጣይ በብልሹ አሰራር ተግባር ውስጥ ገብተው የተገኙ ኦፊሰሮች ላይ አስተማሪ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል አቅም መፈጠሩን በመድረኩ ላይ ተመላክቷል።

በስልጠናው ወቅት የባለስልጣኑ የስነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ እዮብ ከበደ ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመግታት ፓራ ሚሊተሪ ኦፊሰሮችን በእውቀትና በስነ-ምግባር ማነፅ እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል። አክለውም ስልጠናው ከንደፈ ሀሳብ ባሻገር በተግባር የተደገፈ በመሆኑ ህብረተሰቡን በሙያዊ ስነምግባር ለማገልገል ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአስልጣኞች ስልጠና የሰጡት የኮሚሽኑ የስልጠና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጀንበሩ ኢርኮ የደንብ ማስከበር ሥራ በወቅቱን በሙያ ስነ ምግባር በመታነፅና ሙያዊ ግዴታዎችን በመወጣት ከተቋም ባሻገር የከተማውን ሁለንተናዊ ዕድገት መደገፍ አለበት ብለዋል። የደንብ ማስከበር ተግባር ላይ የሚሳተፉት የፓራ ሚሊተሪ ኦፊሰሮች፣ አመራሮችና ባለሙያዎች ቀጥታ ከደንብ ተላላፊዎች ጋር የሚገናኙ በመሆኑ የስነ ምግባር ልዕልናቸውን ጠብቀው ከጥቅም ግጭት ራሳቸውን በማፅዳት ተቋማዊ ትራንስፎርሜሽን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ዳይሬክተሩ አብራርተዋል።

በስነ ምግባር ሚዲያና ኮሙኒኬሽን
ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

አድራሻ
በአራዳ ክ/ከ ወረዳ 1 ቸርችል ጎዳና
ትንሳኤ ህንፃ 4ተኛ ፎቅ
ጥቆማ ለመስጠት
የነፃ ስልክ መስመር
8887
እንዲሁም በመስመር ስልክ
011 126 61 87
011 126 61 72
Addis Ababa Ethics and Anti-Corruption -ፀረ ሙስና
Addis Ababa Ethics Media
aanticoruption@gmail.co

## የኮሚሽኑ አመራርና ሠራተኞች ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን በዘላቂነት ለመደገፍ ቃል ገቡ







የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራርና ሠራተኞች ከሴቶችና ህፃናት ቢሮ ተረክቦ ሲያሳድጋቸው የነበሩ ልጆች ትውውቅ አድርጓል።

በትውውቅ ፕሮግራሙ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ፈቱ ሰማን የኮሚሽኑ አመራርና ሠራተኞች ከሴቶችና ህፃናት ቢሮ ሁለት ህፃናት ተረክበው ድጋፍ ሲያደርጉ መቆየታቸውን ገልፀው የተረከብናቸውን ህፃናት በዘላቂነት መደገፍ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።

በኮሚሽኑ ልጆቹን ለማሳደግ የተመረጡ አናት አምባሳደሮች የኮሚሽኑ አመራርና ሠራተኞች ህፃናቱን ከተረከቡ በኋላ በስምንት ወራት ውስጥ ያከናወናቸውን ዋና ዋና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለሠራተኞች አቅርበዋል። ሪፖርቱን መነሻ በማድረግ ሠራተኞች በሰጡት አስተያየት ለልጆች የተደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ገልፀው በየወሩ የሚሰጣቸው ድጋፍ ካለው የኑሮ ውድነት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት ብለዋል። አያይዘውም ስፖንሰር በመፈለግ ዘላቂነት ያለው ድጋፍ በማድረግ የህፃናት ወላጆችን ማቋቋም እንደሚገባ አመላክተዋል።

## ሙስናን በዘላቂነት ለመከላከል ትውልድን በስነ ምግባር .......

ከገጽ 9 የዞረ

ሆኖ ለመታገልና ለመግታት ሌላዉንም ለማታገል የወጣቱ ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ከዚህ ዉይይት ልምድና ተሞክሮ በመዉሠድ የትዉልዱን አቅምና የተዘረጉ አሰራሮችን እንዲሁም መረጃን እንደሀብት በመጠቀም ሀገርና ትዉልድን መለወጥ ከሁሉም ማህበረሰብ የሚጠበቅ ነዉ ሲሉ ገልፀዋል።

የአዲስ አበባ ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ እናትአለም መለሰ በበኩላቸው፥ መገናኛ ብዙሃን ሙስናን መታገል የዘወትር ተግባራቸው መሆን አለበት ብለዋል። የስነ ምግባር ግንባታና ሌሎች ተግባራትን በሙያቸው አርዓያ በመሆን ሊሰሩ እንደሚገባም ጠቁመዋል። የአዲስ አበባ የስነ ምግባር እና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር መቅደስ ተስፋዬ፥ በስነ ምግባር የታነጸ ትውልድ ለመፍጠር ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን በአግባቡ መወጣት እንዳለባቸው ጠቁመዋል። የጸጥታ እና የፍትህ አካላት እንዲሁም መገናኛ ብዙሃን በቅንጅት ሊሠሩ እንደሚገባም አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ዋና ኃላፊ አቶ ሰይፈ ደርቤ በበኩላቸው ህዝባዊ ፋይዳ ባላቸዉ ሀገራዊ እና ቀጠናዊ አጀንዳዎች ላይ ትኩረት በማድረግ መረጃን ለሀገር ዉስጥና ለተቀረዉ አለም ተደራሽ በማድረግ በርካታ ስራዎችን በመስራት ኃላፊነቱን እየተወጣ የሚገኝ ተቋም መሆኑን ገልፀዉ የዛሬዉም መርሀ ግብር ተቋሙ ሲሳተፍ የሀገራችን ብሎም የመዲናችንን የእድገት ፍላጎት እና ትልም ለማሳካት ትላልቅ እድሎች ያሉን በመሆኑ በትዉልዱ ላይ ይህን እዉን ለማድረግ ሁላችንም የበኩላችንን ልንወጣ ይገባል ብለዋል።

ለውይይት ሶስት እርእሰ ጉዳዮች የቀረቡ ሲሆን በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የመንግስት ተጠሪ ሚንስተር ዲዔታ በሆኑት ምህረቱ ሻንቆ(ዶ/ር) በትዉልድ ግንባታ፤ የአዲስ አበባ ከተማ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ በወ/ሮ እናትአለም መለሰ ስነ ምግባራዊ ትዉልድ በመፍጠር ሂደት የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ድርሻ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር በመቅደስ ተስፋዬ በስነ ምግባር የታነፀ ሙስናን የሚፀየፍ ትዉልድ ለሀገር ግንባታ ያለዉ ድርሻ ላይ ዉይይት ተደርጎባቸዉ ለቀጣይ ስራ ግብዓት መወሰዱ ተመላክቷል ።

## በለውጡ ሂደት በፀረ-ሙስና ትግል የተገኘው ውጤት ......

ከገጽ 1 የዞረ

በመድረኩ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ ሙስናን በመከላከሉ ረገድ የተዘረጉ አሰራሮች አወንታዊ ውጤት እያመጡ መሆኑን ተናግረዋል። ለአብነትም ህዝቡን በማሳተፍ በተከናወኑ ተግባራት ሕግ የተላለፉ በርካታ ሰዎችን ተጠያቂ ማድረግ መቻሉን ጠቁመው፥ ፕሮጀክቶች ላይ ውጤታማ አፈጻጸም መታየቱ ከስራዎች ውጤቶች መካከል ነው ብለዋል። በትምህርት እንዲሁም በሃይማኖት ተቋማት በኩል ሙስናን በተመለከተ ትውልድ የማነጹ ስራ ከፍተኛ ርብርብ እንደሚጠይቅ አብራርተዋል፡፡ የሙስና ወንጀልን መከላከል ለመንግስት አካል ብቻ የሚተው አይደለም ያሉት ከንቲባዋ በለውጡ ሂደት በፀረ-ሙስና ትግል የተገኘው ውጤት ዘላቂ እንዲሆን የህብረተሰቡ ተሳትፎ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ሲሉ ገልጸዋል። የአዲስ አበባ ከተማ የሥነ ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ ኮሚሽኑ ተቋቁሞ ወደ ስራ ከገባበት 2014 ዓ.ም ጀምሮ ሙስናን ለመከላከል የሚረዱ ሰፋፊ ስራዎች መከናወናቸውን ገልጸዋል። የዜጎችን ግንዛቤ ማሳደግ የሚያስችሉ ስራዎች መሰራታቸውን ጠቅሰው የተቋማትን የሙስና ተጋላጭነት በተመለከተ ጥናቶች መካሄዳቸውን አስረድተዋል። በጥናቱ መሰረት ከተቋማት ጋር ውይይት በማድረግ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ማመላከቱን ገልጸው በዚህም ውጤቶች ተገኝተዋል ብለዋል።

ኮሚሽኑ ሙስናን ለመከላከል የሚረዱ ህግና መመሪያዎች ከማውጣት ጀምሮ የተቋማት አቅም ግንባታ ስልጠናዎችም ተደራሽ እየተደረጉ መሆኑን አብራርተዋል።

ከውይይት ተሳታፊዎች መካከል አቶ ንጉሴ ደግፌ የሙስና ወንጀልን ከመሰረቱ ለመግታት የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት አስፈላጊ መሆኑን አንስተዋል። እኔ እንደ ዜጋ ሃላፊነቴን እወጣለሁ የሚለው አስተሳሰብ ሊጎለብት ይገባል ሲሉም ነው የገለጹት። ሌላኛው ተሳታፊ ኑሪ መሀመድ ሲሆኑ አገልግሎትን በሙስና ሳይሆን በህጋዊ መንገድ ብቻ ማግኘት አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን ለዜጎች የማስገንዘቡ ስራ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ብለዋል።

በከተማ ደረጃ በፀረ-ሙስና ትግሉ እስከ ብሎክ ድረስ በመወረድ የዜጎችን ግንዛቤ የማስፋቱ ስራ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባም አጽንኦት ሰጥተዋል። አባገዳ ታከለ ጨመዳ በበኩላቸው በመዲናዋ የኮሪደር ልማትን ጨምሮ የተለያዩ የልማት ስራዎች ስኬት የሚያበረታቱ መሆናቸውን አንስተው፥ በስኬት ሊቀጥሉ የሚችሉት ሙስናን መከላከል ሲቻል በመሆኑ ሁላችንም ወንጀሉን መከላከልና መታገል ይጠበቅብናል ብለዋል። በበዓሉ አከባበር ላይ ኮሚሽኑ ለሚያከናውናቸው የፀረ-ሙስና ትግል አስተዋጽኦ ላበረከቱ አካላት እውቅና ተሰጥቷል።

## ሙስናን በዘላቂነት ለመከላከል ትውልድን በስነ ምግባር .......

ከገጽ 1 የዞረ

በመድረኩ የውይይት መነሻ ፅሁፍ ያቀረቡት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ ምህረቱ ሻንቆ(ዶ/ር)፥ ለሙስና በር ከፋች ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ስራ አጥነት መሆኑን ጠቅሰዋል። በመሆኑም የሞራል ብልሹነትንና ሙስናን ለማስቀረት የስራ ዕድል ፈጠራን ማጠናከር እንደሚገባ አንስተዋል። ትውልዱን በስነ ምግባር ኮትኩቶ ማሳደግ ወሳኝ እንደሆነ በመጥቀስ፥ ትምህርት ቤቶች እና የሃይማኖት ተቋማትም የየራሳቸውን ድርሻ መወጣት እንዳለባቸው አመላክተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የሠላም የፍትህና የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሙሉነህ ደሳለኝ እንደገለፁት ሙስና ትልቅና ሠፊ አጀንዳ የያዘ እንደሀገርም ሌብነትና ብልሹ አሰራር በማህበራዊ በኢኮኖሚና በፖለቲካዊ ለምናደርገዉ ጉዞ ትልቅ ስብራት መሆኑን ጠቅሰዉ ጉዳዩን ለራሳችን እንጂ ለሌላ የሚተዉ አለመሆኑ ይህ ዉይይት ማሳያ ነዉ ብለዋል።

አክለዉም ለበርካታ ዓመታት በከተማ አስተዳር መዋቅር ዉስጥ የፀረ ሙስና ኮሚሽን ያልተቋቋመ እንደነበረ ገልፀዉ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ተቋሙ ህጋዊ እዉቅና ተሰጥቶት ወደ ተግባር መግባቱን ጭምር ገልፀዉ በተደረገዉ ክትትልና ድጋፍ 41 ተቋማት ላይ ጥናት በማድረግ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑና ክፍተት ያለባቸዉ ተለይተዉ በ16 ተቋማት ላይ በተወሰደዉ እርምጃ መሻሻሎች መታየቱና በከተማዋ በትምህርት ተቋማት አስተሳሰብና ልማት ላይ በመስራት በርካታ ለዉጦች እየተመዘገበ መሆኑና ሚዲያዎችም ጅምርና ተስፋ ሰጪ ስራዎችን እየሰሩ ይገኛሉ ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ጀማል ረዲ በበኩላቸዉ ሙስና ሀብትና ንብረት የሚጎዳ ብቻ ሳይሆን የትዉልድ ነፃነትን የሚገፍና ትዉልዱ ማግኘት የሚገባዉን የሚያሳጣ በሀገራት የሚታይ መገለጫ መሆኑን ጠቅሰዉ ይህን ከፊት

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# የትራፊክ ፖሊሶች በስነ ምግባር አርአያ በመሆን ስራዎቻቸውን ማከናወን እንደሚገባቸው ተገለፀ





በስልጠናው ወቅት

የትራፊክ ፖሊሶች በስነ ምግባር አርአያ በመሆን ስራዎቻቸውን ማከናወን እንደሚገባቸው ተገለፀ።

የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ–ሙስና ኮሚሽን ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ ትራፊክ ቁጥጥር ዲቪዥን ጋር በመተባበር በሙያ ስነ ምግባርና ሙስናን መከላከል ላይ ስልጠና ሰጠ።

በስልጠናው ወቅት የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር መቅደስ ተስፋዬ የስራ ላይ ስነ ምግባር ስልጠና ህግ ለሚያስከበር ተቋማት አመራርና ሠራተኞች ወሳኝ መሆኑን ገልፀው የስነ ምግባር ስራችንን ለማከናወን መሰረታዊ ጉዳይ ነው ብለዋል። አያይዘውም የትራፊክ ፖሊስ አባላት በስነ ምግባር አርአያ በመሆን ስራዎቻቸውን ማከናወን እንደሚገባ ገልፀዋል።

የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ትራፊክ ቁጥጥር ዲቪዥን ኃላፊ ኢንስፔክተር ያደታ ሚደቅሳ በክፍለ ከተማችን ከኮሚሽኑ ጋር በመተባበር ስልጠና ሲሰጥ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑን ጠቅሰው ከዚህ ቀደም በወሰድነው ስልጠና በ2016 ያስመዘገብነው ውጤት ምስክር ነው ብለዋል። ክፍለ ከተማው በርካታ ባለስልጣናት፣ ዲፕሎማቶችና አለም አቀፍ ተቋማት መገኛ በመሆኑ ስራችንን በዕውቀትና በስነ ምግባር መስራት ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ስልጠናውን የሰጡት የኮሚሽኑ የስልጠና ክፍል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጀንበሩ ኢርኮ በበኩላቸው የትራፊክ ፖሊስ አባላት ስራቸውን በሙያ ስነ ምግባር ለማከናወን ስልጠናው ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ብለዋል።

የትራፊክ ፖሊስ ስራ አካላዊም ሆነ አእምሮአዊ ብቃት የሚያስፈልገው በመሆኑ አባላቱ ራሳቸውን እያበቁ መሄድ ተገቢ መሆኑን የገለፁት ዳይሬክተሩ የሚመጡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ከሙያ ስነ ምግባር ጋር በማጣጣም ስራቸውን በሚፈለገው ልክ መስራት እንደሚያስፈልግ በሰነድ አብራርተዋል።

# ኮሚሽኑ ከትምህርት ቢሮ ጋር በቅንጅት በሰራቸው ስራዎች እውቅና አገኘ

የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2016 በጀት አመት ባከናወናቸው የትውልድ ስነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራዎች ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ እውቅና አገኙ።




ኮሚሽኑ ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ጋር በቅንጅት ለመስራት በተፈራረመው መሠረት በ2016 በጀት አመት በሰራቸው ስራዎች በተለይም በሁሉም የመንግስት የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ክበባትን በማደራጀት፣ ለክበባት አመራር መምህራንና ተማሪዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት፤ በማጠናከርና ቀጣይነት ያለው የትውልድ ስነ ምግባር ቀረፃ ስራዎች

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የሙስናና ብልሹ አሠራር ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሥነ-ምግባር ግንባታ ሥራ ማጠናከር ይገባል፤

በከተማው የሙስናና ብልሹ አሠራር ተጋላጭነትን ለመቀነስ ሕብረተሰቡን ያሳተፈ የሥነ-ምግባር ግንባታ ሥራውን አጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዲስ አበባ ከተማ ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ።

ኮሚሽኑ የ2016 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም መሠረት በማድረግ በየደረጃው ላሉ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች እውቅናና ሽልማትም ሰጥቷል።

በመድረኩ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የሰላም፣ ፍትሕና መልካም አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ሙሉነህ ደሳለኝ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ጥላሁን ወርቁ፣ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ጀማል ረዲና ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።



ኮሚሽኑ በትውልድ ሥነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራ ላይ እያከናወነ ያለው ተግባር አበረታች መሆኑን በመድረኩ ላይ ንግግር ያደረጉት በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የሰላም፣ ፍትሕና መልካም አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ሙሉነህ ደሳለኝ ገልፀዋል። አዲስ አበባን የኢትዮጵያ ብልፅግና ተምሳሌት ማድረግ የሚቻለው ሙስናና ብልሹ አሠራርን በቁርጠኝነት በመታገል በመሆኑ፤ ሥራው በተቀናጀ አግባብ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

ኮሚሽነር ጀማል ረዲ በዚሁ ወቅት እንዳሉት፤ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ተቋሙ ተልዕኮውን ሊያሳካ የሚችል ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በመንደፍ በሥነ ምግባር ግንባታና ሙስናን በመከላከል ውጤታማ ተግባራት ተከናውኗል ሲሉ ተናግረዋል።

በሥነ ምግባር ግንባታና በሙስና መከላከል ላይ ሥልጠና መስጠት፣ ጥቆማ የመቀበልና የማጥናት፣ ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከልና የኅብረተሰቡን የሙስና ግንዛቤ ማሳደግ ላይ በትኩረት መሰራቱን ኮሚሽነሩ ጠቅሰው በዚህም የመንግሥትና የሕዝብ ሃብትን ከምዝበራ የማዳንና እርምጃ የማስወሰድ አቅም ማደጉን ተናግረዋል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በአስቸኳይና በመደበኛ የሙስና መከላከል ሥራ 3 ነጥብ 5 ቢሊየን የሚጠጋ ብር ከምዝበራ ማዳኑን ገልፀው በ2017 በጀት ዓመትም ይህን በማጠናከር በትውልድ ሥነ ምግባር ግንባታና ሙስናን የመከላከል ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ እንዳይሆኑ ጥናትን መሠረት ያደረገ የአሠራር ሥርዓት የማሻሻል ተግባር እንደሚከናወን የተናገሩት ኮሚሽነሩ ተቋሙ የሀገርና የሕዝብን ንብረት ከምዝበራ ለማዳን በሚያደርገው ጥረት ሕዝቡ የበኩሉን ሚና እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።







# የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን
# ፎቶ ቅኝት














አድራሻ:- በአራዳ ክ/ከ ወረዳ 1 ቸርችል ጎዳና ትንሳኤ ህንፃ 4ተኛ ፎቅ ጥቆማ ለመስጠት የነፃ ስልክ መስመር 8887
እንዲሁም በመስመር ስልክ 011 126 61 87 እና 011 126 61 72

በስነምግባር ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ